# የገቢዎች ሚኒስቴር
# መመሪያ ቁጥር 3/1996

## ከቀረጥ ነፃ የገቡ ዕቃዎች ለሌላ ወገን በሚተላለፉበት ጊዜ የዕርጅና ቅናሽ ስለሚታሰብበት ሁኔታ የወጣ መመሪያ

ከቀረጥ ነፃ ሆነው ወደሀገር የገቡ ዕቃዎች አገልግሎት የዕርጅና ዘመን ቅናሽን በተመለከተ የመብቱ ተጠቃሚ በሆኑ ሰዎች መካከል ልዩነት ሳይደረግ አንድ ወጥ በሆነ መልኩ ለመፈፀም እንዲቻል ይህን መመሪያ ማውጣት አስፈልጓል::

### 1. አውጭው ባለሥልጣን

የገቢዎች ሚኒስቴር የጉምሩክ ባለሥልጣንን ለማቋቋምና አሠራሩንም ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 60/1989 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 84/2 መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል::::

### 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ «ከቀረጥ ነፃ የገቡ ዕቃዎች ለሌላ ወገን በሚተላለፉበት ጊዜ የዕርጅና ቅናሽ ስለሚታሰብበት ሁኔታ የወጣ የገቢዎች ሚኒስቴር መመሪያ ቁጥር 3/1996» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### 3. ትርጓሜ

1. «የቀረጥ ነፃ ተጠቃሚ» ማለት በሕግ ወይም በመመሪያ ዕቃዎችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆነው ለማስገባት የተፈቀደለት ወይም የቀረጥ ነፃ መብት ያለው ማናቸውም ሰው ነው::
2. «ዕቃ» ማለት ማንኛውም የመጓጓዣ ተሽከርካሪ፣ መሣሪያ ፣ የቢሮ መገልገያና የግል መገልገያ ዕቃ ነው::
3. «መንግሥት መ/ቤት» ማለት ማናቸውም በበጀት የሚተዳደር የመንግሥት መ/ቤት ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅት ነው::
4. «ተሽከርካሪ» ማለት በሞተር ኃይል በመንገድ የሚንቀሳቀስ የሰውና የጭነት መጓጓዣ ከነመለዋወጫው ሲሆን ብስክሌትንም ይጨምራል::
5. «መሣሪያ» ማለት ማንኛውም የማምረቻና የአገልግሎት መስጫ የካፒታል ዕቃ ነው::

ጌታቸው በላይ
ሚኒስትር

35

6. «የመቅረጫ ዋጋ» ማለት ዕቃው ወደ ሀገር ውስጥ በገባበት ጊዜ የነበረው የሲ.አይ.ኤፍ ዋጋ ነው::

7. «የግል መገልገያ» ማለት ለግል የቤት ውስጥ አገልግሎት የሚውል ዕቃ ሲሆን ተሽከርካሪዎችንና የቢሮ መገልገያ ዕቃዎችን አይጨምርም::

8. የጉምሩክ ባለሥልጣንን ለማቋቋምና አሠራሩንም ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 60/89 (እንደተሻሻለ) የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል::

## 4. የመመሪያው የተፈፃሚነት ወሰን

1. የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች ቀረጥ ሳይከፈልባቸው ለመንግሥት መ/ቤት አገልግሎት ወደሀገር ውስጥ በመጡና በጊዜያዊነት ወደሀገር ውስጥ በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም::

2. ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት ከቀረጥ ነፃ ተደርገው በአገልግሎት ላይ ያሉና ቀረጥ ሳይከፈልባቸው የቀረጥ ነፃ መብት ላላቸው ባለመብቶች በተላለፉ ዕቃዎች ላይ ጭምር ተፈፃሚነት ይኖረዋል::

## 5. ከቀረጥ ነፃ የገቡ ዕቃዎችን ስለማስተላለፍ

1. የጉምሩክ ባለሥልጣንን እንደገና ለማቋቋምና አሠራሩንም ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 60/89 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 54 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ በተመለከተው የዕርጅና ቅናሽ ስሌት መሠረት ከቀረጥ ነፃ የገቡ ዕቃዎችን የቀረጥ ነፃ መብት ለሌለው ሰው ማስተላለፍ ይቻላል::

2. የዕቃው የእርጅና ቅናሽ ስሌት የሚታሰበው በዕቃው የመቅረጫ ዋጋ ላይ ሆኖ ዕቃው ወደአገር ውስጥ ከገባበት ቀን አንስቶ ይሆናል::

## 6. የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ስለሚከፈልበት ሁኔታ

1. ማንኛውም የቀረጥ ነፃ ተጠቃሚ የሆነ ሰው ወደሀገር ውስጥ ከቀረጥ ነፃ ያስገባው ወይም ከቀረጥ ነፃ እንዲሆን የተደረገው ዕቃ የእርጅና ዘመን ከማለቁ በፊት የቀረጥ ነፃ መብት ለሌለው ሰው ሲያስተላልፍ ከዚህ በታች በተመለከተው ሠንጠረዥ አንድ፣ ሁለት፣ ሦስትና አራት መሠረት የእርጅና

ጌታቸው በላይ
ሚኒስትር

36

ቅናሽ ምጣኔው በመቅረጫ ዋጋ እና ፀንቶ ባለው የታሪፍ ልክ መሠረት ቀረጡ ታስቦ ይከፈላል:: ሆኖም የመቅረጫ ዋጋቸው ብር 3,000.00 (ሦስት ሺህ) እና ከዚያ በታች የሆኑ የግል መገልገያ ዕቃዎች ለሌላ ሦስተኛ ወገን ሲተላለፉ ቀረጥና ታክስ አይከፈልባቸውም::

2. የዕቃው አገልግሎት በሙሉ ዓመት በማይገለፅበት ጊዜ ዕቃው የገባበትን ቀን መሠረት በማድረግ መንፈቅ እና ከዚያ በላይ ያገለገለ ከሆነ ብቻ ወደ ቀጣዩ ዓመት በማስጠጋት የአገልግሎት ዕድሜው እንዲታሰብ ይደረጋል::

3. ከቀረጥ ነፃ የገባው ዕቃ የዕርጅና ዘመኑ ከማለቁ በፊት እንደ እሳት ቃጠሎ፣ የግጭት አደጋ በመሳሰሉት ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበት ከሆነ፣ ባለበት ሁኔታ ለማስተላለፍ አግባብ ባለው ባለሙያ ወይም ተቋም ተገምቶ የተገኘው ዋጋ የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ተደርጎ ይወሰዳል::

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም የቀረጥ ነፃ ተጠቃሚው ከቀረጥ ነፃ የገባው ዕቃ የዕርጅና ዘመን ከማለቁ በፊት ለመንግሥታዊ መ/ቤት በስጦታ የሚያስተላልፈው ከሆነ ቀረጥ እንዲከፍል አይጠየቅም:: ሆኖም የጉምሩክ ባለሥልጣን ስጦታው የተላለፈለትን መ/ቤት ማንነት፣ የዕቃውን ዓይነት ዝርዝርና ዋጋ እንዲሁም ሲከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ ልክ መዝግቦ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ያሳውቃል::

## ሠንጠረዥ አንድ
## የግል መገልገያዎች የዕርጅና ቅናሽ ስሌት

| ወደ ሀገር ከገባ በኋላ የአገልግሎት ዘመን | የአገልግሎት ዘመን ቅናሽ መቶኛ በአንዱ ዕቃ መቅረጫ ዋጋ ላይ | |
|---|---|---|
| | መቅረጫው ዋጋ ከ3,000 ብር በላይና ከ10,000ብር በታች ከሆነ | መቅረጫ ዋጋው ብር 10,000 እና ከዚያ በላይ የሆነ እንደሆነ |
| 1 ዓመት | 25 ከመቶ | 20 ከመቶ |
| 2 « | 50 « | 40 « |
| 3 « | 75 « | 60 « |
| 4 « | 100 « | 80 « |
| 5 « | - | 100 « |

ጌታቸው በላይ
ሚኒስትር

Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Revenues

37

## ሠንጠረዥ ሁለት
## የተሽከርካሪዎች የዕርጅና ቅናሽ ስሌት

| የአገልግሎት ዘመን አገር ውስጥ ከገባ በኋላ | የአገልግሎት ቅናሽ መቶኛ በመቅረጫ ዋጋ |
|---|---|
| 1 ዓመት | 10 |
| 2 « | 20 |
| 3 « | 30 |
| 4 « | 40 |
| 5 « | 50 |
| 6 « | 60 |
| 7 « | 70 |
| 8 « | 80 |
| 9 « | 90 |
| 10 « | 100 |

## ሠንጠረዥ ሦስት
## የቢሮ መገልገያዎች የዕርጅና ቅናሽ ስሌት

| የአገልግሎት ዘመን በአገር ውስጥ | የአገልግሎት ቅናሽ መቶኛ በመቅረጫ ዋጋ |
|---|---|
| 1 ዓመት | 20 |
| 2 « | 40 |
| 3 « | 60 |
| 4 « | 80 |
| 5 « | 100 |

ጌታቸው በላይ
ሚኒስትር

## ሠንጠረዥ አራት

## የመሣሪያዎች የዕርጅና ቅናሽ ስሌት

| የአገልግሎት ዘመን አገር ውስጥ ከገባ በኃላ | የአገልግሎት ቅናሽ መቶኛ በመቅረጫ ዋጋ ላይ |
|---|---|
| 1 | 0 |
| 2 | 5 |
| 3 | 10 |
| 4 | 20 |
| 5 | 30 |
| 6 | 40 |
| 7 | 50 |
| 8 | 60 |
| 9 | 70 |
| 10 | 80 |
| 11 | 90 |
| 12 | 100 |

7. <u>መረጃ ስለመያዝ እና በተጠየቀም ጊዜ ስለመስጠት</u>

1. የጉምሩክ ባለሥልጣን ከቀረጥ ነፃ የሚገባ ማንኛውንም ዕቃ የመቅረጫ ዋጋው ሦስት ሺ(3,000.00) ብር እና ከዚያ በታች ከሆነው በስተቀር በጽሑፍ መዝገብ ወይም በኤሌክትሮኒክስ መሣሪያ(በኮምፒዩተር) መዝግቦ ይይዛል:: የመረጃው መዝገብ ቢያንስ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ ይኖርበታል::

ሀ. የአስመጪው ወይም የቀረጥ ነፃ ተጠቃሚው ሙሉ ስምና አድራሻ

ለ. የጉምሩክ ዲክላራሲዮን ቁጥርና ቀን

ሐ. የዕቃው ዓይነት ሞዴል፣ የተሠራበት አገር

መ. የሲ.አይ.ኤፍ ዋጋ በአሜሪካን ዶላር

ጌታቸው በላይ
ሚኒስትር

39